## በቮልዩም ፡ ፰ ፡ ቁ. ፩ ለወጡት ፡ የቤተሰብ ፡ ሕግ ፡ ጥያቄዎች ፡ መልሶች ።

በኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ መጽሔት ፡ ላይ ፡ ወጥተው ፡ ለነበሩት ፡ ለመጀመሪያው ፡ ጥያቄ ፡ መልስ ፡ በማቅረብ ፡ ያሸነፉት ፡ ከአሥመራ ፡ አቶ ፡ አብርሃም ፡ ክብሮም ፡ ናቸው ። ለመጀመሪያው ፡ ፕሮብሌም ፡ ያቀረቧቸው ፡ በጣም ፡ ጥሩዎቹ ፡ መልሶቻቸው ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ ታትመዋል ። የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ መጽሔት ፡ ቮልዩም ፡ ፱ና ፡ መልሱ ፡ የተጻፈባቸው ፡ ተጨማሪ ፡ እትሞች ፡ ለጸሐፊው ፡ በነፃ ፡ ይደርሳቸዋል ።

የጥያቄው ፡ ደራሲ ፡ ፕሮፌሰር ፡ ቹቹኖቪች ፡ የሰጡት ፡ መልሶች ፡ ማወቅ ፡ ለሚፈልጉ ፡ ሁሉ ፡ በተጨማሪ ፡ ታትመዋል ።

### ፩. የአቶ ፡ አብርሃም ፡ ክብሮም ፡ መልሶች ።

ለአንደኛ ፡ ጥያቄ ፡ መልስ ፡

ዝምድና ፡ ያስገኘው ፡ ጋብቻ ፡ ቢፈርስም ፡ ዝምድናው ፡ ይኖራል ፡ የሚለው ፡ የፓርላማው ፡ ቅየራ ፡ አንቀጽ ፡ ፭፻፶፭ ፤

፩ኛ. ጋብቻው ፡ ቢፈርስም ፤ የጋብቻ ፡ ዝምድና ፡ ባላቸው ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ ጋብቻ ፡ እንዳይፈጸም ፡ ከልክሎታል ። አንቀጽ ፡ ፭፻፹፫ ፤

፪ኛ. የዝምድናው ፡ መተሳሰር ፡ በፍች ፡ ምክንያት ፡ ሲቀር ፤ ቀለብ ፡ የመስጠት፡ ግዴታውም ፡ ቀሪ ፡ እንዲሆን ፡ አድርጎታል ። አንቀጽ ፡ ፮፻፶፱ ፤

### ፪. ከጆርጅ ፡ ቹቹኖቪች ፡ የተሰጡ ፡ መልሶች ።

በውድድሩ ፡ ውስጥ ፡ ሳይሳተፉ ፡ ወይም ፡ የውድድሩን ፡ ውጤት ፡ ሳይነኩ ፡ የጥያቄዎቹ ፡ ደራሲ ፡ ለአራቱ ፡ ፕሮብሌሞች ፡ የሚከተሉትን ፡ መልሶች ፡ ይሰጣሉ ።

#### ፕሮብሌም ፡ ፩

ጥያቄ ፡ ፩ ፤

የተለወጠው ፡ ሕግ ፡ ውጤት ፡ (ያልተለወጠውን ፡) ቁጥር ፡ ፭፻፹፫ ፡ ከጋብቻ ፡ መፍረስ ፡ ውጭ ፡ ውጤቶችን ፡ ማራዘም ፡ ነው ።

ጥያቄ ፡ ፪ ፤

የተለወጠውን ፡ ሕግ ፡ ውጤት ፡ (ያልተለወጠውን ፡) ቁጥር ፡ ፮፻፮(፩) ከጋብቻ ፡ መፍረስ ፡ ውጭ ፤ ከፍች ፡ በስተቀር ፡ (ቁ. ፮፻፱ ፡) ያሉ ፡ ውጤቶችን ፡ ማራዘም፡ ነው ።

#### ፕሮብሌም፡ ፪ ፤

ጥያቄ ፡ ፩ ፤

ተደራራቢ ፡ ነው ፡ የሚባለው ፡ አባባል ፡ ትክክል ፡ ነው ። ምክንያም ፡ የቁ. ፮፻፶፪ አጻጻፍ ፡ ከቤተሰቦች ፡ ወይም ፡ ከመንግሥት ፡ (ኑዛዜ ፡ ሳይኖር) ሌላ ፡ ሁሉም ፡ ሰዎች ፡

ከመውረስ ፡ ተገልለዋል ። ለምሳሌ ፤ ምንም ፡ እንኳን ፡ ስለዚህ ፡ ሁኔታ ፡ የተወሰነ ፡ ሕግ ፡ ባይኖርም ፤ ከተጋቢዎች ፡ አንዱ ፡ ከመውረስ ፡ ተገልሏል ። በቁባት ፡ (ከጋብቻ ፡ ውጭ ፡ በግብረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት) ፡ ረገድ ፡ የዚህ ፡ ዓይነት ፡ ሕግ ፡ መኖር ፡ ለሕጉ ፡ ምንም ፡ አይጨምርለትም ፡- ቁ. ፯፻፲፫ ተደራራቢ ፡ ነው ።

ጥያቄ ፡ ፪ ፤

ውሳኔው ፡ ስህተት ፡ ነው ። ምክንያት ፡— ቅርሱን ፡ የፈጠረው ፡ ኑዛዜ ፡ ወይም ፡ ውርስ ፡ የተባለው ፡ ሕጋዊ ፡ ድርጊት ፡ እንጂ ፡ "ከጋብቻ ፡ ውጭ ፡ የግብረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት" ፡ ባለመሆኑ ፡ የቁ. ፯፻፲፫ ፡ ሕግ ፡ አልተጣሰም ።

## ፕሮብሌም ፫ ፤

ጥያቄ ፡ ፩ ፤

ቁጥር ፡ ፳፻፺፩(ሐ) የሚመለከተው ፡

ሀ) የጋብቻን ፡ ውጤቶች ፡ ሳይሆን ፤ ሕጋዊ ፡ ጋብቻ ፡ የሚፈጸሙበትን ፡ ሁኔታዎችና ፤

ለ) የጋብቻ ፡ ሩካቤ — ሥጋ ፡ ግንኙነት ፡ ሳይሆን ፤ ሩካቤ — ሥጋ ፡ ለመፈጸም ፡ ባለመቻል ፡ ሌላው ፡ ተጋቢ ፡ የሚፈጽመው ፡ ስህተት ፡ ነው ።

ጥያቄ ፪ ፤

ቁጥር ፡ ፯፻፺፯(፫) የሚመለከተው ፡ የጋብቻ ፡ ውጤቶችን ፡ ሳይሆን ፡ የጋብቻ ፡ መፍረስን ፡ ነው ።

## ፕሮብሌም ፡ ፬ ፤

"በኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ዋጋ ፡ ስለሌላቸውና ፡ ፈራሽ ፡ ጋብቻዎች" ፡ የኢት. ሕግ ፡ መጽሔት ፡ (፲፱፻፷፭ ፡ ዓ. ም.) ፤ ቮልዩም ፡ ፰ ፤ ቁጥር ፡ ፪ ፡ በኬ. አዶኖቫን ፡ በተሰጡት ፡ ምክንያቶች ፡ መሠረት ፡ የአራተኛውን ፡ ቁጥር ፡ ሐሳብ ፡ እንመርጣለን ።